ሐምሌ 28/2015

# የአማራ ህዝባዊ መንግስት ምስረታ

በአንድ አማራ ንቅናቄ ተዘጋጂቶ የቀረበ
ምዕራፍ 2 ሰነድ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| የአማራ ህዝባዊ መንግስት አመሰራረት | 4 |
| 1. የወረዳ፡ ዞን እና ክልል መንግስት አመሰራረት | 5 |
| 1.1. በአንድ ወረዳ ህዝባዊ መንግሥት የመመስረት አካሄድ፡- | 5 |
| 1.2. የዞን አማራዊ መንግስት አመሰራረት | 7 |
| 1.3. የክልል መንግስት አመሰራረት | 9 |
| 2. የጠላት አሰላለፍ | 10 |
| 3. የትግል መስመሮች | 11 |
| 3.1. የብሔር ፖለቲካ መስመር / ብሄር ፌደራሊዝም | 11 |
| 3.2. የዜጋ ፖለቲካ መስመር | 13 |
| 4. የአማራን ትግል የሚጠልፉ የብአዴን ክንፎች | 15 |
| 4.1. የንግዱን ሰንሰለት የተቆጣጠረው ብአዴን | 15 |
| 4.2. ተጠባባቂው ብአዴን | 15 |
| 4.3. ሃይማኖታዊ ብአዴን | 16 |
| 4.4. ደላላው ብአዴን | 16 |
| 4.5. የብአዴን የዳያስፖራ ክንፍ | 17 |
| 5. አድቮኬሲ/Advocacy | 18 |
| 6. ንቅናቄ | 20 |
| 7. የጦር ኃይል / Military | 22 |

በዛሬዉ እለት ሐምሌ 28/2015 የአንድ አማራ አደረጃጀት የትግል ፍኖተ ካርታ በይፋ አዉጥቷል፡፡ ይህን ጥራዝ ያወጣበት ምክንያት የአማራ ፋኖ ህዝቡን ማስተዳደር ማገልገል ያለበት በመሆኑ የፖለቲካ እና አስተዳደር ሃይል ሆኖ ለመደራጀት የማደራጃ ጥራዝ በማስፈለጉ ነዉ፡፡ የአንድ አማራ አደረጃጀት ተጨማሪ የመተንትን ጥራዞችን ለፋኖ አካላት በእጅ የሚያደርስ ይሆናል፡፡

# የአማራ ህዝባዊ መንግስት አመሰራረት

የአማራው የትግል ምዕራፍ መስመር እየያዘ በመምጣቱ ትግሉ የራሱ የሆነ ፍኖተ ካርታ ያስፈልገዋል። ትግል ፍኖተ ካርታ ወይም መዳረሻ ከሌለው በድርድር የሚቋጭ ይሆናል። የአማራው ትግል ለምሳሌ ከዚህ በፊት ከነበረው የኦሮማራ ጥምረት ጀምሮ ብዙ ድሎችን ቢያገኝም ፍኖተ ካርታ ያልነበረውና መዳረሻው ያልተቀመጠ በመሆኑ ትግሉ በቀላሉ መጠለፍ ችሏል አሁንም የተጀመረው ትግል ተመሳሳይ አደጋ እንዳይገጥመው ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ይፈልጋል ለዚህም ትግሉ በፍኖተ ካርታ መቃኘት ይኖርበታል። ለዚህም በዘላቂነት መፍትሔው አማራዊ መንግሥት በመመስረት ህዝቡ የሚያምንበት ወኪል መፍጠር ነው ። መሪ የሌለው ህዝብ መጨረሻው ለተጨማሪ እንግልትና መጥፋት የተጋለጠ መሆኑ ታምኖ መሪ መፍጠር ጊዜ የማይሰጠው መዳረሻ ነው።

አብዛኞች በአማራ ትግል መሪ ነን ብለው ቢያስቡም በስልጣን ላይ ሆኖ የማያስተዳድር ማንኛውም ታጋይ መሪ ሳይሆን ትክክለኛ መጠሪያው ታጋይ ወይም አታጋይ ይባላል። በአማራዊ አገላለፅም ፋኖ እንለዋለን። ስለዚህ የአማራ ህዝባዊ መንግሥት ለመመስረት ህዝቡን የሚወክሉ አባላት በመፍጠር የፍኖተ ካርታው አካል በመሆን ይህ ረቂቅ ተዘጋጅቷል።

የአማራ ክልል በብዙ ወረዳዎች የተዋቀረ በመሆኑ በነዚህ ወረዳዎችና የክልል ከተሞች ላይ ከፋኖና በትግሉ አስተዋፅኦ ካደረጉ አካላት ጋር በየወረዳው ህዝባዊ አስተዳደር መመስረት ያስፈልጋል። ይህም በመንግሥት ከሚገኙ ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚ ፣ ህግ አስፈፃሚ ውስጥ ህግ አውጪውን የሚተካ ይሆናል። የአማራው ማህበረሰብ በመከራ ውስጥ የቆየ መሆኑ የትግሉን ሃይል እንደ አይኑ ብሌን ሊጠነቀቅለት ይገባል። ይኸውም ምንም አይነት ወንጀል በህዝብና በንብረት ላይ እንዳይፈፀም መጠበቅ ያስፈልጋል። የብአዴን ሃይሎች ህዝቡ በፋኖ ላይ ምሬት እንዲኖረው በማድረግ በህዝቡ ላይ ከግድያ ጀምሮ ብዙ ወንጀሎችን ስለሚሰሩ ይህንን በከፍተኛ ጥንቃቄ መከታተል ፣መጠበቅና መመከት ያስፈልጋል።

# 1. <u>የወረዳ፡ ዞን እና ክልል መንግስት አመሰራረት</u>

## 1.1. በአንድ ወረዳ ህዝባዊ መንግሥት የመመስረት አካሄድ:-

የወረዳውን ምክር ቤት ቁጥር ልክ የሚሆን የሰው ኃይል ከፋኖና ታማኝ ታጋዮች ፣ የእምነት አባቶች የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግሥት ማቋቋም ቀዳሚ ሲሆን ለዚህም ህዝባዊ ውይይት በማድረግ ተመራጮችን ማቅረብ ለህዝቡም ማስተዋወቅ ይኖርበታል ይህም ምርጫ ፊርማ በማሰባሰብ የሚጠናቀቅ ሲሆን የተመረጠው ኃይል ተደጋጋሚ ውይይቶችንና ትውውቆችን በማድረግ የህዝቡን ችግር በመረዳት የአመራር ብቃቱን ማሳየት

ይኖርበታል፡፡ የተሰበሰበው ፊርማ በመጨረሻ ፓርቲ ለመመስረት ስለሚያስፈልግ በአግባቡ ተሰንዶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

የህግ አስፈፃሚ ወይም ፀጥታ ዘርፍን ፋኖ ተቆጣጥሮ ማህበረሰቡን የትጥቅ አጠቃቀም እና ሌሎችን ወታደራዊ ስልጠናዎች በመስጠት ለቀጣይ ትግል የተዘጋጀ ወረዳ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የፖሊስ አካላትን የተሃድሶ ስልጠና በመስጠት በላያቸው ላይ ተቆጣጣሪ በመመደብ ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲገቡ ማድረግ፡፡

ማንኛውንም ለጦርነት አቅሙ የሚፈቅድ አማራ ከስድስት ሳምንት ያልበለጠ ስልጠናዎችን መስጠት የፋኖ ትልቁ ድርሻ ይሆናል፡፡

በአመራር ክህሎት አቅም ያላቸው የፋኖ አባላት የአስተዳደር ወንበር ይዘው የወረዳ ቢሮዎችን ከነፖሊስ ቢሮ መምራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የታጠቀ፣ ህዝባዊ ተቀባይነት ያለው ፣ ጠንካራ የፋኖ መንግሥት ያለበት ወረዳ መፍጠር ያስችለናል፡፡

## 1.2. የዞን አማራዊ መንግስት አመሰራረት

በአማራ ክልል 11 ዞኖች ሲኖሩ እነዚህ ዞኖች ተጠሪነታቸው ለክልሉ ነው፡፡ ይህ ዞን ስልጣኑ ከወረዳ የሚመነጭ በመሆኑ በእያንዳንዱ ዞን የሚገኙ ወረዳዎች ወኪሎቻቸውን በመላክ በዞን ለሚገኙ ቢሮዎች ተመራጮችን መልምሎ በመላክ በእያንዳንዱ ዞን ያሉ ቢሮዎችን የማስተዳደር ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ለዞን አስተዳደርነት የሚመጣ የወረዳ ወኪል የመጣበት ወረዳ ወኪል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆን የተረጋገጠ ፊርማ ይዞ መምጣት ይኖርበታል፡፡ በአንድ ዞን ውስጥ ከታች የተቀመጡት ቢሮዎችን የሚያሟሉ የፋኖ፣ የመንግሥት አካላት በመተካት ለቦታው የሚመጥኑ እጩዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

የዞን አመራሩ በየወረዳው እየዞረ ውይይቶችንና ከማህበረሰቡ ጋር ትዉዉቅ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ በዚህም የሃብት ስብሰባ በማካሄድ የክልሉን የበጀት ክፍተት ማስተካከልና ነፃ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ የወጣት አደረጃጀቶችን በመፍጠር በበጀት ማነስ ምክንያት የሚፈጠሩ ክፍተቶችን የሚሞላ አደረጃጀት መፍጠር ማህበረሰቡ ላይ የሚፈጠረውን ጫና ይቀንሳል፡፡

እያንዳንዱ ወረዳ ይሄን ሃይል በማደራጀት ሃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡ ይህ የዞን አመራር በስሩ የሚገኙ ወረዳ አስተዳደሮች ተናበውና ተዋውቀው የሚሰሩበትን መንገድ በመፍጠር በየወረዳው የሚካሄደውን የፀጥታ ኃይል ግንባታና ስልጠና በትኩረት መደገፍ ይኖርበታል ምክንያቱም አዲስ ለሚፈጠረው የአማራ ህዝባዊ መንግሥት የጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያግዝ በመሆኑ ነው፡፡

1. የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ
2. የዞኑ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ
3. የግብርና መምሪያ ኃላፊ
4. የንግድና ትራንስፖርት መምሪያ ኃላፊ
5. የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት መምሪያ ኃላፊ
6. የገንዘብና ኢኮኖሚልማት መምሪያ ኃላፊ
7. የውሃ ሃብት ልማት መምሪያ ኃላፊ
8. የአካባቢ ጥበቃ፣የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ ኃላፊ
9. የትምህርት መምሪያ ኃላፊ
10. የጤና ጥበቃ መምሪያ ኃላፊ
11. የፍትህ መምሪያ ኃላፊ
12. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ
13. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
14. የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት መምሪያ ኃላፊ

*15.* የሲቪል ሰርቪስ ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ

*16.* የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ

*17.* የቴክኒክና ሙያ መምሪያ ኃላፊ

## 1.3. የክልል መንግስት አመሰራረት

የክልል ቢሮዎች የዞን ውጤቶች ሲሆኑ ሁሉም ዞን አቅም አለው የሚለውን አመራሩን ወደ ክልል መላክ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ከዞኑ ምክር ቤት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተመርጦ መምጣት አለበት፤ ይህም ተአማኒነት ያለው መንግሥት ለመመስረት ያግዛል፡፡ የክልል አመራርና ማዕከላዊ ኮሚቴ እንደተሟላ ከየወረዳው የተሰበሰቡ ፊርማዎችን ይዞ በይፋ አማራዊ መንግሥት ፓርቲ ይመሰረታል፡፡ ይህም ጠንካራ የወታደራዊ ክንፍ ይዞ መንግስት ይህናል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ የትውውቅ መግለጫዎችን በማውጣት ለሌላውም ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖረው ብሄር ብሄረሰብ በማብሰር ሁለተኛውን የትግል ምእራፍ የሚጀመር የአማራ ህዝባዊ መንግሥት ይሆናል፡፡

የክልል ቢሮዎች በፓርቲው ማኒፌስቶ ከነመተዳደሪያ ደንቡ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

## 2. የጠላት አሰላለፍ

አማራውን በጠላትነት ፈርጀው የተመሰረቱ የ60 ዎቹ ኃይሎች ብአዴን፤ ኦነግ እና ወያኔ፤ ዛሬ ላይ የታጠቁ ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ያላቸው ኃይሎችን ፈጥረዋል። ከዚህም ባለፈ ብሔራዊ ፕሮጀክት ተሸክመው መወለዳቸው መቼም የማይታረቅ ህልም በአገሪቷ ላይ የተሸከሙ አደረጃጀቶች መሆናቸው የአማራውን ትግል ከባድ እና መራራ ያደርገዋል። ስለዚህም የገጠመንን ፈተና ፊት ለፊት መግጠም ግዴታ ሆኖ አግኝተነዋል። አማራን እንደ ሕዝብ ጠላት አርገው የፈረጁ ኃይሎች በሙሉ፤ ለአማራ ህዝብ ጠላት መሆናቸው ታውቆ መጥፋት ወይም ራሳቸውን ማከሰም ይኖርባቸዋል።

በ1986 ዓ.ም የብአዴን ማኒፌስቶ አማራን በጠላትነት የፈረጀ ሲሆን በመሰልጠኛ ሰነዶቹ ውስጥ ሳይቀር አማራ ጠል ትርክቶች በጥልቅ ተፅፈው ይገኛሉ። ሌላው የህወሃት ኦነግ እና የኦህዴድ ብልፅግና የአማራን ህዝብ በጠላትነት በመፈረጅ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ናቸው። እነዚ ኃይሎች በዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲሁም የአማራ ማህበረሰብ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ሰርቶ እንዳይኖር፣ እንዳይቀየር ከፍተኛ ወከባ እየፈጠሩ ያሉ ኃይሎች ናቸው። እነዚህ አራት አደረጃጀቶች በእኩል ደረጃ ለአማራው ህዝብ የህልውና አደጋ መሆናቸው ታምኖ በጠላት አሰላለፍ ላይ የመጀመሪያውን ረድፍ ይይዛሉ። አማራው እነዚህ አራት ሃይሎች ላይ ተመሳሳይ

አቋም ሊኖረው ይገባል፡፡ ከመሃላቸው የተሻለ አለ ብሎ ማሰብ የመጥፊያን በር መክፈት ይሆናል፡፡ በጠላት ላይ የጋራ አቋም የሌለው ማህበረሰብ ራሱን ለሰርጎ ገቦች ያጋልጣል፡፡ የሚመሰርታቸው አደረጃጀቶች የመሰለል እድላቸው ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ ይሄ ደግሞ በቀላሉ አደረጃጀቶች እንዲከስሙ ምክንያት ይሆናል፡፡ በጠላት አሰላለፍ ላይ ያልተስማማ የትኛውም አደረጃጀት አብሮ ሊሰራ እንደማይችል ሊሰመርበት ይገባል፡፡

## 3. የትግል መስመሮች

በኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት አይነት የትግል መስመሮች ወይም አሰላለፎች አሉ፡፡

### 3.1. የብሔር ፖለቲካ መስመር / ብሄር ፌደራሊዝም

ይህ አሰላለፍ የብሄር ክልሎችን የፈጠረና የአማራ የግዛት አካባቢዎችን አንድነት እውን በማድረግ የሚረዳ በህዝብ ቁጥር ላይ የተመሰረተ በየትኛውም ከአማራ ክልል ውጪ ባለ ክልል ፖለቲካዊ ውክልና በማግኘት በያለበት የአገር ባለቤት የሚሆንበት እና ከፌዴሬሽን ምክር ቤት እስከ ተወካዮች ምክር ቤት የህዝብ ቁጥሩን ተጠቅሞ ፖለቲካዊ ውክልና የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ አማራው የግዛት አንድነቱን ለማስጠበቅ የብሔር ፌደራሊዝም አይነተኛ የአደረጃጀት መንገድ ነው፡፡ ይህም ማህበረሰቡን በሃሳብና በአካል ለመሰብሰብ

ይጠቅመዋል። አማራው በታሪኩ ፌደራሊስት በመሆኑ በቀላሉ ከዚህ ስርዓት ጋር ለመዋሃድ ጊዜ አይፈጅበትም። የግዛት አንድነቱ የተጠበቀ የህዝብ ቁጥሩን እንደ ኃይል የሚጠቀም ሃቀኛ አመራር ያለው ማህበረሰብ የህዝቡን ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ቀላል ይሆንለታል። አማራው በክልሉ የሚገኙ እንደ አባይ ወንዝ ያሉ ሃብቶች ስላሉት ነገውን ብሩህ ያደርጉለታል። የግዛት አንድነቱን ካስጠበቀ ቀላል የማይባል ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ በአፍሪካ መፍጠር ይችላል። በናይጄሪያ የሚገኘው የኢቦ ማህበረሰብ በአለም ደረጃ የሚታወቅ የሃብት እንቅስቃሴው ከናይጄሪያ ባሻገር ጠንክሮ እናገኘዋለን። የብሔር ፌደራሊዝም በሌለበት እንደ አማራ ተደራጅቶ የስልጣን ባለቤት መሆን አይቻልም። ከክልሉ ውጪ ያለውም አማራ ራሱን በልዩ ዞኖች ፣ወረዳዎች፣ ቀበሌዎች እና የከተማ ካቢኔ ካደራጀ በዋታላ በክልሉ ከሚገኘው አማራ ጋር ጠንካራ አንድነት ያለው የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ትስስር መፍጠር ይቻላል። የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ግንኙነት ትስስር በእጅጉ የላላ በመሆኑ አማራው እንደ አማራ ተደራጅቶ መቀጠሉ ጠንካራ መህበረሰባዊ አንድነት እንዲኖረው ይረደዋል። ለዚህም በፖለቲካ እንደ አማራ መደራጀቱ ግዴታ እና አማራጭ የሌለው የህልውና መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን። በተጨማሪም በብሔር መደራጀትን እንደ ነፃ መውጣት የተቀበሉ ብሔር/ ብሔረሰቦች ኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸው ይታወቃል፤ ስለዚህ በዚህ አደረጃጀት መቆየታችንን ማስረገጫ ሆኖ እናገኘዋለን። የአንድ አማራ አደረጃጀት ይህንን መንገድ መጠቀም ከፍተኛ የሆነ

ከጂኦ ፖለቲካዊ እስከ ሃገራዊ አካሄዶች ላይ አዉንታዊ ፖለቲካዊ ሚና ይጫወታል። በእጃችን ላይ ያለው ወጣትም የዚህ አስተሳሰብ አስቀጣይ ሆኖ ማግኘታችንን በማሰብ፤ ይህን የትግል መንገድ በጥብቅ ይመክራል።

## 3.2. የዜጋ ፖለቲካ መስመር

ይህ አሰላለፍ በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዲሁም ብሔር ብሔረሰቦች ተቀባይነት የሌለው ሲሆን አላማውም የትኛውም ብሔር በማንነቱ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳይኖረው የሚያግድ ይሆናል። ይህ ማለት የአማራ ክልልን የሚያፈርስ እንዲሁም ሌሎች ክልሎችንም የሚያፈርስ ሲሆን አማራዊ የግዛት ጥያቄዎች ተናንሰው በወንዜነት ጥያቄዎች የሚቀየሩ ይሆናል ። በቅርቡ በተጠናከረው አማራዊ አንድነት ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያደርስ ሲሆን እርስበርስ የግዛት ግጭቶች በማስነሳት እስካሁን የገነባነውን አንድነት የሚያፈርስ ይሆናል። ይህም የሚከናወነው በሌሎች ጠንካራ ብሔርተኝነት ባነገቡ ህዝቦች መጫወቻ ሜዳ ላይ ይሆናል። አንድነቱን ያጣ ማህበረሰብ በየእጥፋቱ ለብዙ አስርተ አመታት በተደራጀ ህዝብ መሃል መንቀሳቀስ የመጥፊያውን ደወል በራስ ላይ መደወል ይሆናል።

በዚህ አደረጃጀት መንገድ ከአማራ ክልል ውጪ ያለውን አማራ በተደራጀ ማህበረሰብ መሃል ታግሎ ጥቅሙን ለዛውም እንደግለሰብ ሆኖ እንዲያስከብር መተው አደጋውን እጅግ የከፋ ያደርገዋል። ይህ መስመር አዲስ

ያልሆነና ከዚህም በፊት የተሞከረ ነው፡፡ በደርግ ሥርዓት ወቅት የነበረና ለብዙ ተገንጣይ ኃይሎች መስፋፋት ምክንያት የሆነ ሥርዓት ነው፡፡ የብሄርተኝነት ትጥቁን የፈታ ማህበረሰብ መሆናችን ባለፉት 50 አመታት ብሄርተኝነትን በታጠቁ አካላት የበላይነት እንዲያዝብን ከዛም አልፎ የህልውና አደጋ ላይ እንድንወድቅ ሆኗል፡፡ የህልውና አደጋውን የቀለበስንበትን ፖለቲካዊ ብሄርተኝነት አፋፍመን በመሄድ የኢኮኖሚ አቅማችንን እንድንገነባ ይሄን የብሔርተኝነት ትጥቅ የሚያስፈታንን መንገድ መከተል አይኖርብንም፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ ከከተማ 14% ነዋሪ በስተቀር ይህን አደረጃጀት የሚደግፍ አንድም ብሔር ባለመኖሩ ይሄን መንገድ መከተል ለአማራው ጠላትን መግዛት ይሆናል፡፡ በአሁን ጊዜ ወላይታ ፣ ጉራጌ ሌሎችም ብሔሮች የፖለቲካ ውክልና በሚጠባበቁበት ወቅት ወደ ዜጋ ፖለቲካ የመሄድ እንቅስቃሴ ማድረግ ውሃን ሽቅብ እንደማፍሰስ ይቆጠራል፡፡ ይህንንም መተግበር እጅግ ከባድ ሲሆን ለመተግበርም ከነዚህ ሁሉ ብሔርተኛ ኃይሎች ጋር ተጋፍጦ ማሸነፍን ይጠይቃል፡፡ በብዙ መስዋዕትነት አሸናፊነት ቢገኝ እንኳን ትርፉ ፖለቲካዊ አማራነትን መስበር ከዛም ባለፈ የግዛት አንድነታችንን በመሸርሸር አማራው እርስበእርሱ የሚናከስበትን ክፍተት መውለድ ይሆናል፡፡ ይህንን በማስተዋል የዜጋ ፖለቲካን እንደ ኢዜማ ላሉ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች መተው ይገባል፡፡

# 4. የአማራን ትግል የሚጠልፉ የብአዴን ክንፎች

የአማራን ህዝብ ትግል የሚጠልፉ አምስት የብአዴን ክንፎች አሉ።

## 4.1. የንግዱን ሰንሰለት የተቆጣጠረው ብአዴን

ይሄ ሃይል የፖለቲካ ተሳትፎ የለውም በአብዛኛው ቀጥታ ከገበሬው ጋር ነው ግንኙነት ያለው ይኸውም ምርት ከገሬው በርካሽ ገዝቶ ለአገር ውስጥ እና ለውጪ ነጋዴዎች በውድ ዋጋ የሚሸጥና ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ሃይል ነው በመሆኑም የብአዴን መወገድ በቀጥታ ከጥቅሙ ጋር ስለሚገናኝ ብአዴን እንዳይወድቅ በተቻለው መጠን ትግል በመጥለፍ ይሳተፋል።

## 4.2. ተጠባባቂው ብአዴን

ስልጣን ላይ የለም ግን ማንኛውንም አጋጣሚዎች ሁሉ ይጠቀማል ከበላይ ባለስልጣናት ጋር እየተላላከ ስልጣን የሚጠብቅ ሃይል ነው። ህዝብ ውስጥ በመግባት የተሻለ የብአዴን አመራር አለ በማለት የማዘናጋት ስራ ይሰራል።

## 4.3. ሃይማኖታዊ ብአዴን

የአማራ ህዝብ በሃይማኖት የታነፀ ማህበረሰብ በመሆኑ ብአዴን እንደድክመትና ትግል ለመጥለፍ የሚጠቀምበት ትልቁ መሳሪያ የእምነት አባቶቸን ነው። ይሄ ሃይል ግጭቶቸ ሲፈጠሩ ቁርአንና ታቦት ይዞ አስታራቂ በመምሰል የብአዴንን እድሜ የሚያራዝም ነው። እዚህ ውስጥ ቄሶቸ ፣ ሼሆቸና ፓስተሮቸ እንዲሁም ሽማግሌዎቸ ይገኙበታል።

## 4.4. ደላላው ብአዴን

ይሄ ሃይል ባለሃብቱንና ፖለቲከኛውን አካል ድልድይ ሆኖ የሚያገናኝ ዋነኛው ትግል ጠላፊ ክንፍ ነው።

## 4.5. የብአዴን የዳያስፖራ ክንፍ

ይህ አደረጃጀት በአማራ ተቃውሞ ውስጥ የመሪነት ሚና የሚጫወት ሲሆን ትግልን የማቀጣጠል መልሶም የማጨናገፍ ስራ የመስራት ኃላፊነት ከእናት ፖርቲው ከብአዴን ተሰጥቶት የሚንቀሳቀስ ነው። አደረጃጀቶችን በመዋጥ Controlled opposition እንደ ትግል tactic ይጠቀማል። በሶቬት ዩኒዬን በቦሎሾቪክ ፖርቲ (Bolshevic party) ቅኝት የተገለበጠ በሚመስል "If you want to control an opposition, you should be the one leading it" ይህን ብሂል መሬት ላይ ተግብሮት እናገኘዋለን። ለዚህም የመሬት ስጦታ፣ የጎጥ ወዳጅነት፣ የኢንቨስትመንት ድጋፎችን በመስጠት ከብአዴን ጋር በቀጥታ ካልሆነ ከብአዴን የካዱ ተብለው በብአዴን የድርብ ወኪል (double agent) ሚና በተሰጣቸው አካላት የሚዘወር ይሆናል።

## **5. አድቮኬሲ /Advocacy**

ይህ ኃይል ዋና ሚናው የአማራውን በደል ለአለም አቀፍ ማህበረሰብ ማሳወቅ ነው። ይሄን ለማድረግ ከጋዜጠኞች እና ከሁሉም የትግል ኃይሎች ጋር ተናቦ መስራት አለበት። አብዛኛው የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በምእራባዊ ሀገራት የተመሰረቱ እና የሚገኙ በመሆናቸው ድምፃችን እንዲሰማ ከነዚህ ሀገራት ብሔራዊ ጥቅም ጋር በሚስማማ መልኩ አድቮኬሲው መሰራት ይኖርበታል።

አድቮኬሲ በአውሮፓ በተባበሩት መንግሳታት: በአሜሪካ ደግሞ ከስቴት ዲፓርትመንትና / **state department** እና ኮንግረስ ሴኔት ቢሮ **Congress/Senate office** ጋር የሚደረግ ሲሆን በአውሮፓ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ላይ ጠንካራ ስራ መሠራት ይኖርበታል።

በአሜሪካ የሚደረገው አድቮኬሲ ከአውሮፓ የሚለየው ፖለቲካዊ ጫና መፍጠሪያ መሆኑ ኑው። አሜሪካ የምስራቅ አፍሪካን  ፖለቲካ በንቃት ከመከታተል አልፎ የአንጋሽነት ሚና ያላት በመሆኑ በአሜሪካ የሚሰራው አድቮኬሲ እጅግ የሰላ የፖለቲካ አረዳድ ባላቸው መሆን ይኖርበታል። የአሜሪካ ብሔራዊ ጥቅም የማይቀያየር በመሆኑ በጥበብ የአማራውን የፖለቲካ አቅምና በደል ማሣየት ይኖርበታል።

አሜሪካ ኢትዮጵያን እንደ ብሔር ሀገርና የተፎካካሪ ሀይሎች መቀመጫ አድርጋ የምታይ በመሆኑ ይህም ብሔርተኛ ሆኖ ፖለቲካን መስራት አዋጭ መንገድ ያደርገዋል። ሌላው ይህን ለማሳካት አቅም ስለሚያስፈልግ ከፍተኛ በሆነ የሰልፍና ሌሎች እንቅስቃሴዎች መደገፍ ይኖርበታል። ስለዚህ በየስቴቱ ያሉ አደረጃጀቶች ራሳቸውን ችለው ይህን መተግበር ይኖርባቸዋል። በአውሮፓም በአሜሪካም ስም ያላቸው ውጤት ያስመዘገቡ ተከራካሪ ጠበቃ መግዛት ግዴታ ነው። ከዚህም ባለፈ ጠንካራ ጋዜጠኞችን በማሠለፍ በተለያዩ ሚዲያዎች የፊት ገፅ ትኩረት ማግኘት ያስፈልጋል።

## 6. ንቅናቄ

የንቅናቄ ዋናዉ ሚና ሁሉንም የያዘ የትግል እንቅስቃሴ ማድረግ ነዉ። ይህ አደረጃጀት ህዝባዊ መሰረትን በአግባቡ የሚጠቀም ስለሆነ በየአከባቢው ያለን የአማራ ህዝብ የትግል አጋር በማድረግ አብዮቱን የሚያቀጣጥል ኃይል ነዉ።

ከትጥቅ ክንፉ ዉጪ ያለው የእዝ ሰንሰለቱ እጅግ ቀላል የሆነ ለስራ የሚመች መሆን ይጠበቅበታል ። አመራሮቹን ማሳወቅ አደረጃጀቱን አደጋ ላይ ስለሚጥል የህቡዕ ስራዉን ማከናወን ይኖርበታል ። ይህ ኃይል የህዝብ ቁጥርን እንደ ትልቅ አቅም የሚጠቀም በመሆኑ የሚያገኛቸዉን የመልእክት ማስተላለፊያ መንገዶች በሙሉ መጠቀም ይኖርበታል ።

ለዚህም የ **PR** (ፕሮፓጋንዳ ) ሥራ የሚሰሩ እጅግ የሰላ አእምሮ ፣ ተግባቢ ፣ግርማ ሞገስ እና የህዝብን ቀልብና ልብ በቀላሉ በሚይዙ ግለሰቦች መዋቀር ይኖርበታል ። ይህ ክንፍ እንደ ጦር ጫፍ ሲሆን ዋናዉን የትግል ጫፍ የሚቀድ ኃይል ሆኖ እናገኘዋለን።

ይህ ኃይል መደራጀት ያለበት ለህዝባቸዉ እጅግ ታማኝና ተቆርቋሪ  በሆኑ ግለሰቦች መሆን ይኖርበታል ምክንያቱም በግል ጥቅምና ዝና መስመር የሳተ እንዳሆነ አደጋዉ ከባድ ስለሚሆን ነው ። የጥንቃቄን ሚና በትክክል በተረዱ አመራሮች መምራት የጥንቃቄዉን ተደራሽነት ያሰፋዋል ።

ይህ ኃይል አጀንዳዎችን በየጊዜዉ እየቀረፀ ወደ ተግባር ከሚቀይረው ክንፍ ጋር ተናቦ የሚሰራ ሲሆን ከፍተኛ የፓለቲካ ጥበብ እና የጠላትን ኃይል አሰላለፍ በእጅጉ በተረዳ መንገድ መንቀሳቀስ ይኖርበታል ። በአጠቃላይ እንቅስቃሴው የአማራዉን አሸናፊነት ቀድሞ የሚያበስርና በዚህም የሚከሰቱ ስጋቶችን ቀድሞ በመጋፈጥ አጋጣሚዎችን በአግባብ የሚጠቀም ኃይል መሆን ይኖርበታል ።

## 7. የጦር ኃይል / Military

አማራዉ ከገባበት የከበባ ሁኔታ ሰብሮ ለመዉጣት የጦር ሀይሉን ማደራጀት ቀዳሚ የሆነ ተግባር ነዉ። በአማራ ክልል ብቻ እጅግ ብዙ የትጥቅ አደረጃጀቶች በመኖራቸዉ እነዚህን ሀይሎች በአንድ መስመር በማሰለፍ ተናበዉና ተረዳድተዉ እንዲሰሩ በማድረግ አሸናፊነትን መጎናፀፍ ይቻላል። በየወረዳዉ በየከተማዉ እና በዞን ደረጃ የተደራጁ ፋኖዎች በአንድ የእዝ ሰንሰለት ማሰለፍ እና ሃብትንና የሰዉ ሀይልን በላቀ ደረጃ ለመጠቀም ይረዳል። ለዚህም ጠንካራ ወታደራዊ ሀይል ያስፈልጋል Political and discipline indoctrination ክፍፍሎች ሲኖረዉ ሁሉም የፋኖ አደረጃጀት በዚህ ተመሳሳይ ጥራዝ መሰልጠኑ ተናቦ ለመስራት  ግቡንም አንድ አድርጎ ለመጓዝ ከዛም በላይ ጥፋቶች ቢኖሩ ቅጣቶችን ለመተግበር ይረዳል። በአንድ መሰልጠኛ ጥራዝ የሰለጠነ ሠራዊት በቀላሉ አብሮ ለመስራት እንዲችል ስለሚያደርገዉ ይህንን ጥራዝ በፍጥነት ለሁሉም አደረጃጀቶች ማሰራጨት ለነገ የማይባል ተግባር ነዉ ። አደረጃጀቶቹ ከስር የተዘረዘሩ ሲሆን የፖለቲካዊ ምርጫ በማዘጋጀት ላይ የአንድ አማራ አደረጃጀት ናሙና የሚያቀርብ ይሆናል።

ይህን ጥራዝ ተከትሎ ከሚወጣው (ምዕራፍ 3 ) ሰነድ ውጪ ሌሎች ጥራዞችን የአንድ አማራ ንቅናቄ የማያውቃቸው መሆናቸውን አንባቢው እንዲረዳ እንመክራለን፡፡ በዚህ ጥራዝ ማህበረሰቡ እንዲሰበሰብ ታስቦ ፍፁም ይፋዊ በሆነ መንገድ በአንድ አማራ ንቅናቄ የማህበራዊ ትስስር ገፆች አዲለቀቅ ተደርጓል፡፡

## የአማራ ህዝባዊ መንግስት ሰነድ

# ድል ለአማራ ህዝብ!